**ኖቨምበር 2017 QuickNotes ፈጣን መልእክት ቁ. 3**

**የትምህርት ቦርድ $1.83 ቢሊዮን የካፒታል ባጀት አፀድቋል።**

<Summary:> **ይህ የስድስት-ዓመት እቅድ በትምህርት ቤቶች ያለውን የመጣበብ ሁኔታ እና እያረጁ ያሉ ሕንፃዎችና መገልገያዎችን ችግር ለማቃለል ይረዳል።**
**ቦርዱ በሪቻርድ ሞንጎመሪ እጅብ/ክለስተር** (Richard Montgomery cluster) **አንደኛ ደረጃ ት/ቤት አዲስ የድንበር/የወሰን እቅድ መርጧል።**

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የተማሪዎች ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ ምክንያት የህዝብ ት/ቤቶችን የቦታ መጣበብ ለማቃለል እና እያረጁ ያሉትን ሕንፃዎች/መገልገያዎች እድሳት ለማድረግ የ$1.83 ቢሊዮን ዶላር የስድስት-ዓመት የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም** (CIP) **የባጀት ጥያቄ በአንድ ድምፅ አፀድቋል። የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራሙ 30 አዳዲስ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክቶችን ይጨምራል።**

**ለ 2017-2018 የትምህርት ዓመት የተማሪዎች ቁጥር 161,936 ይሆናል። በአንድ ዓመት የተማሪዎች ቁጥር በ2,926 ይጨምራል። ባለፉት 10 ዓመታት፣ የተማሪዎች ምዝገባ ቁጥር በ 24,191 ጨምሯል።**
**የትምህርት ቦርድን ውሳኔ ያንብቡ።**

**የትምህርት ዋና ተቆጣጣሪ/ሱፐርኢንተንደንት ያቀረቡትን የበጀት ዓመት 2019 ካፒታል በጀት እና የ2019-2024 ካፒታል ያንብቡ** (FY 2019 Capital Budget and the FY 2019–2024 Capital)

**በተጨማሪም፣ ቦርዱ በሪቻርድ ሞንጎመሪ እጅብ/ክለስተር** (Richard Montgomery cluster) **ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት አዲስ የድንበር/የወሰን እቅድ መርጧል። ት/ቤቱ በ 2018 በልግ/ፎል ላይ ይከፈታል።**
**የድንበር/የወሰን እቅዱን ይመልከቱ**

**ሪፖርት ካርዶች ኖቬምበር 22 ተሰራጭተዋል፣ ምን ያህል አዳዲስ ነገሮች እንዳሉበት ማወቅ አለብዎት።**

<Summary:> ለ 2017-2018 የትምህርት ዓመት በውጤት/ማርክ አመዘጋገብ እና በካርዶቹ ላይ ምን ያህል ለውጦች እንደተደረጉ ይወቁ።

ለተማሪዎች የሪፖርት ካርዶቹ የተሰራጨት ኖቬምበር 22 ነው። የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ወላጅ ከሆኑ፣ በልጅዎ የሪፖርት ካርድ ላይ ትላልቅ ለውጦች መደረጋቸውን ተገንዝበው ይሆናል። በዚህ ዓመት MCPS ስለ ሪፖርት ካርድ እና የውጤት መመዘኛ ክለሳ/ለውጥ አድርጓል። ክለሳ የተደረገበት ምክንያት ትምህርትን ለተማሪዎች ይበልጥ ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ እና ስለ ትምህርት ክህሎትና ስለ ሥራ እውቀት ልምድ ተጨማሪ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለመስጠት የተነደፈ ነው። ለውጡ ወላጆች፣ የት/ቤት ሠራተኞች፣ እና ማህበረሰቡ ያደረጓቸውን አስተዋፅዎች ያንፀባርቃል።

**ምን አዲስ ነገር አለ?**

- ከ2ኛ–5ኛ ክፍሎች A, B, C, D
- የምዋእለ ህፃናት ተማሪዎች በዓመት (ከሁለት ጊዜ ይልቅ) አራት ጊዜ የሪፖርት ካርድ ያገኛሉ።
- (የዓመት-መጨረሻ አማካይ ውጤት እና ከእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ወቅት መለኪያ ርእሶች ላይ በተጨማሪ) የአጠቃላይ ትምህርት ውጤትን ያካትታል።
- ቁልፍ የመማር ክህሎቶችን ሪፖርትም ያካትታል።

ስለ ሪፖርት ካርዶች ለመረዳት የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን እዚህ ይገኛል።

ስለ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ሪፖርት ካርዶች ላይ ስለተደረጉት ለውጦች መረጃ/ኢንፎርሜሽን እዚህ ለማግኘት ይችላሉ።

የእርስዎን ተማሪ ሪፖርት ካርድ በሚከተለው የኢንተርኔት መስመር ሊመለከቱ እንደሚችሉ ያስታውሱ። myMCPS Parent Portal

**በክረምት/ዊንተር የእረፍት ጊዜ "የተማሪ የሥራ አገልግሎት ትምህርት" ሰዓት ያጠራቅሙ።**

<Summary:> የክረምት/ዊንተር የእረፍት ጊዜ "ለተማሪዎች የሥራ አገልግሎት ትምህርት ፕሮጀክት" ሰዓት ለማጠራቀም በሥራ የሚሳተፉበት እድል ይሰጣቸዋል። እና በመጀመሪያው ሴሚስተር ላይ ያገኙትን የሥራ አገልግሎት ሠዓቶች ጃኑዋሪ 5, 2018 ለት/ቤት የማስረከቢያ ቀን መሆኑን ያስታውሱ።

የክረምቱ እረፍት ጊዜ በሥራ አገልግሎት ትምህርት ፕሮጀክት ለመሳተፍ እና "የተማሪ አገልግሎት ትምህርት" ሠዓቶችን ለማግኘት/ለማጠራቀም ትልቅ እድል ይፈጥራል። ለሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (MCPS SSL) ተቀባይነት ያላቸውን ድርጅቶች እና ያሉትን እድሎች ያጣሩ/ይመልከቱ። እና፣ በመጀመሪያው ሴሚስተር የተገኙት "የተማሪ አገልግሎት ትምህርት" ሠዓቶች በጠቅላላ ለት/ቤት SSL አስተባባሪ ከዓርብ ጃኑዋሪ 5, 2018 አስቀድሞ መቅረብ እንዳለበት ያስታውሱ።

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት

## የማርቲን ሉተር ኪንግ የስነጥበብ (ቪዡዋል አርትስ) ውድድር ለMCPS ተማሪዎች በሙሉ ክፍት ሆኗል/ተጀምሯል።

<Summary:> ውድድሩ በማንኛውም የክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች ክፍት ነው። የስነጥበብ ሥራዎቹን እስከ ዓርብ፣ ዲሴምበር 15 ማቅረብ ያስፈልጋል።

በዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር የስነጥበብ ሥራ (ቪዡዋል አርትስ) ውድድር በሁሉም የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች እንዲሳተፉ እናደፋፍራለን። የ 2018 ፍሬ ሀሳብ/ጭብጥ "ከፍያለ ተስፋ/ግብ—A ለማሟላት ትላንት፣ ዛሬ፣ እና ነገን ማክበር"። ተማሪዎች የወደፊት ራዕያቸውን/ህልማቸውን ምን እንደሆነ በስነጥበብ እንዲተረጉሙት ተጠይቀዋል።

በውድድሩ ላይ:- የህትመት ሥራዎችን፣ ሥዕላዊ ፖስተሮችን፣ባለቀለማት ነገሮችን በመለጣጠፍ የተሰሩ ሥዕሎችን/የኮላዥ ጥበብ፣ የግድግዳ ሥዕሎችን፣ ፎተግራፎችን እና ሌሎችም (መጠን ስፋት ጥልቀት) ለመለካት የሚቻል ሁለት-ዳይሜንሽን የስነጥበብ ሥራ ቅርጾችን ለማቅረብ ይቻላል። (The contest is open to prints, posters, collages, murals, photographs, and all other two-dimensional visual art forms). የቡድን ሥራ ፕሮጀክቶችም ተቀባይነት አላቸው። መወዳደሪያዎችን ለLinda S. Adams, supervisor, Pre-K-12 Fine Arts, Carver Educational Services Center, Room 258, 850 Hungerford Dr., Rockville, MD 20850 ይላኩ። የመጨረሻው ቀን **ዓርብ፣ ዲሴምበር 15 5 p.m ነው።** The deadline is 5 p.m. on Friday, Dec. 15.

የመወዳደሪያ መሥፈርት መመዘኛዎችን የሚያሟሉ የስነጥበብ ሥራዎች ሰኞ፣ ጃኑዋሪ 15 በማሪቲን ሉተር ኪንግ የመታሰቢያ ቀን ስትራትሞር የሙዚቃ ማዕከል/Music Center at Strathmore ለእይታ ይቀርባሉ። ከዚያ በመቀጠል ሮክቪል በሚገኘው የሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ሕንፃ ውስጥ የአፍሪካን-አሜሪካን ታሪክ መዘከሪያ የሚከበርበት ፌብሩዋሪ ወሩን በሙሉ ለእይታ ይቀመጣሉ።

የማርቲን ሉተር ኪንግ ስነጥበብ ሥራዎች መወዳደሪያ በራሪ ጽሑፍ/ፍላየር
LINK TO PDF

## የMCPS ተማሪዎች ያገለገሉ አውቶሞቢሎችና ፣ የኮምፒውተሮች ሽያጭ ያከናውናሉ

<Summary:> ሽያጭ የሚካሄደው ቅዳሜ፣ ዲሴምበር 9 በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ነው። The sale will be held on Saturday, Dec. 9 at Gaithersburg High School. መኪናዎቹ እና ኮምፒውተሮቹ በተማሪዎች አማካኝነት ለመማሪያነት ተሟልተው የተስተካከሉ/የታደሱ ናቸው።

በሞንጎመሪ ካውንቲ የአውቶሞቲቭ ትሬድስ ፋውንዴሽን (ATF) እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፋውንዴሽን (ITF) ተማሪዎች በርካታ ያገለገሉ አውቶሞቢሎችን እና ኮምፒውተርቾችን ጠግነው/አስተካክለው **ቅዳሜ ዲሴምበር** 9 በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከ 9–11 a.m ለሽያጭ ያቀርባሉ። የጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኘው በሚከተለው አድራሻ ነው:-

101 Education Blvd in Gaithersburg.

ለሽያጭ ስለሚቀርቡት ኮምፒውተሮች የበለጠ መረጃ ለማግኘት:- በስልክ ቁጥር 240-740-2048 ደውለው ለመጠየቅ ይችላሉ።

ስለ አውቶሞቢሎች የበለጠ ለማወቅ በስልክ ቁጥር 240-740-2047 ይደውሉ፣ ወይም Mike Snyder ን ያግኙ። ለሽያጭ የቀረቡት መኪናዎች/አውቶሞቢሎች ዝርዝር እዚህ ይገኛል።
Michael_c_snyder@mcpsmd.org
www.cars2purchase.org

መኪናዎቹ እና ኮምፒውተሮቹ በክፍል እና ላቦራቷር ለመማሪያነት ያገለገሉና በተማሪዎች አማካይነት ተሟልተው የተስተካከሉ ናቸው። አውቶሞቢሎቹ/መኪናዎቹ የሜሪላንድ ስቴት ቁጥጥር/ኢንስፔክሽን የተደረገላቸው እና አብዛኞዎቹ ከሽያጩ ቦታ በቀጥታ ወደቤት ለመነዳት የሚችሉ ናቸው። ሽያጮቹ ለተማሪዎች ስለሽያጭ/sales skills/ ችሎታና ልምድ እንዲቀስሙ እድል ይሰጣቸዋል፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሠዓት ያስገኙላቸዋል፣ ስለ ማህበረሰብ ተሳትፎ ጠለቅ ያለ እድናቆት እንዲኖራቸው እድል ይሰጣቸዋል።

የማህበረሰብ አባላት ለፕሮግራሙ ተሽከርካሪዎችን እንዲለግሱ በአክብሮት እንጠይቃለን። የልግስና ተሽከርካሪዎችን automotive ፕሮግራም ባላቸው በ Damascus፣ Gaithersburg፣ Seneca Valley ወይም Thomas Edison የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች ለመስጠት ይቻላል። ጠቅላላ የልግስና-ስጦታዎች ታክስ ተቀናሽ ናቸው።

የአውቶሞቢሎች ንግድ ስራ ተቋም (Automotive Trades Foundation)
http://www.cars2purchase.org/

የመረጃ ቴክኖሎጂ በጎአድራጎት (Information Technology Foundation)
http://www.itfcareers.org/